# የቅንጅት ካናዳ ቋሚ ምክር ቤት እና የሥራ አመራር አካል ምስረታ በሚመለከት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ግንቦት 1999

በተለያዩ የካናዳ ክፍለ ሀገራት እና ከተሞች የቅንጅትን ራዕይ አንግበን ስንንቀሳቀስ የቆየን ቻፕተሮች ዛሬ ሜይ 17 2007 ዓመተ ምህረት የካናዳ አቀፍ ቋሚ ምክር ቤት በመመስረት ፣ የምክር ቤቱን የሥራ አመራር አካል ግልፅ እና ነፃ በሆነ ዲሞክራሲያዊ የድምፅ አሰጣጥ አግባብ በመሰየም የምክር ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ አፅድቀናል።

በቅንጅት ካናዳ ማዕከል የስራ አመራር ምስረታ ጉባዔ ላይ የተሳተፍነው የቅንጅት ቻፕተሮች፡

- ቅንጅት ቶርንቶ
- ቅንጅት ቫንኩቨር
- ቅንጅት ካልገሪ
- ቅንጅት ዊንፔግ
- ቅንጅት ዋተርሉ

ቀደም ሲል የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ሲያከናውን የቆየው የቅንጅት ካናዳ ጊዜያዊ አስተባባሪ አካል

1ኛ የቋሚ ምክር ቤቱን ደንብ በማርቀቅ ፣
2ኛ ረቂቁን ለየቻፕተሮቹ ሥራ አስፈፃሚ አካላት እንዲደርስ እና በተለያየ የመገናኛ ዘዴ ተከታታይ ውይይቶች እንዲደረጉበት በማድረግ፣
3ኛ ረቂቁን ለማሻሻል የተሰጡትን አስተያየቶች አጠናቅሮ ለመጨረሻ ውሳኔ በማቅረብ
4ኛ በመጨረሻም የቅንጅት ካናዳ የሥራ አመራር አባላት ምርጫ ዲሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ እንዲከናወን በማመቻቸት የተጣለበትን አደራ በብቃት ተወጥቷል፤

በተካሄደው የምክር ቤት የሥራ አመራር ድልድል አሥራ አንድ አባላትን ያቀፈ እና ከሁሉም ድጋፍ ቻፕተሮች የተወከሉ አባላትን ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል። የማዕከሉ ዋና ጽሕፈት ቤት ቶሮንቶ ላይ እንዲሆን የወሰነው ይኸው ጉባዔ በመጭው እሁድ ግንቦት 20 2007 የምክር ቤቱ የሥራ አመራር አባላት የመጀመሪያ ስብሰባ በጽሕፈት ቤቱ እንዲከናወን ወስኗል። በዚሁ ዕለት በቅንጅት ቶሮንቶ የተጠራ ሕዝባዊ ስብሰባ የሚካሄድ መሆኑ ይታወቃል። በዚሁ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ለመገኘት የሁሉም ቻፕተሮች ተወካዮች እና ከየቻፕተሮቹ የተመረጡ የሥራ አመራር አባላት ከዓርብ ግንቦት 18 2007 ጀምሮ ቶሮንቶ ይገባሉ።

ግንቦት 97 መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲ ስርዓት መስፈን ፣ ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ እንዲሁም ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሲል በሰላም ድምፅ የሰጠበት እና ድሉን በወያኔ ተሰርቆ ከመረጣቸው መሪዎቹ ጋር ግዙፍ መስዋዕት እየከፈለ የሚገኝበት ልዩ አጋጣሚ ወቅት መሆኑ የስብሰባችንን ታሪካዊነት ያጎላዋል።

ከሁለት ዓመታት በፊት ግንቦት ወር ቅንጅትን በፖለቲካ መሪነት በይፋ አደባባይ ወጥቶ የመረጠው ወገናችን ፍላጎቱ ብረትን መከታ ባደረገው ወያኔ ቢቀማም ትግሉ ያበሰረውን ፅኑ ዲሞክራሲያዊ ፍላጎት ከቶውንም አፈና ሊያቀመው እንደማይችል ቅንጅት ካናዳ በፅኑ ያምናል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት 97 ሰላማዊ ሕዝባዊ ድል ባረጋገጠው የቅንጅት ራዕይ እየተመራ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚያደርገውን ትግል በሁሉም ዘርፍ እናግዛለን። ቻፕተሮች ከዚህ ቀደም ባልተቋቋመባቸው የተለያዩ የካናዳ ከተሞች የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የተፈጠረውን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ተጠቅማችሁ በያካባቢያችሁ እንድትሰባሰቡ ፣ ድጋፍ የምትሹ ጽ/ቤታችንን ለመገናኘት ጥረት እንድታደርጉ በዚህ ታሪካዊ ዕለት ጥሪ እናቀርባለን።

በሕዝብ ድምፅ መመረጣቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ኢፍትሐዊ በደል እየተፈፀመባቸው ያሉት የቅንጅት መሪዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ በሁሉም መስክ የሚደረገውን ትግል ለማጠናከር ሌት ተቀን ሳንል ለመሥራት ቃል እንገባለን። ከዚህም በላይ በአገራችን የተንሰራፋውን ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ረገጣ ለማስቆም ብሎም የቅንጀትን ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ትግል ይበልጥ በማራመድ እና የዜግነት ድርሻችንን ለመወጣት በሙሉ ልብ መሰለፋችንን እንደገና በዛሬይቱ ግንቦት እናረጋግጣለን።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የቅንጅትን ራዕይ አንግበን ወደድል ጎዳና እናመራለን!!!

**ቅንጅት ካናዳ ድጋፍ ማእክል**
**ሜይ 17 2007**